# በአራዳ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ፅ/ቤት

# የ6ኛ ክፍል ሞዴል ግብረ ገብ ፈተና

# ጥር 2017 ዓ.ም /2025 እ.ኤ.አ

የጥያቄ ብዛት ፡- 30 የተፈቀደው ሰዓት ፡-1 ሰዓት

**አጠቃላይ ትዕዛዝ ፡-**

ይህ የግብረ ገብ ፈተና 40 ጥያቄዎች የያዘ ነው፡፡ እያንዳንዱ ጥያቄ አራት አራት አማራጮች ያሉት ሲሆን ለእያንዳንዱ ትያቄዎች ከያዙት አራት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ የመረጡትን ፊደል በቀጥታ ለመልስ መስጫ በተሰጠው ወረቀት ላይ በእርሳስ በሚገባ በማጥቆር መልሱ ማስቀመጥ ይኖርባችኋል ፡፡

ፈተናውን ሰርቶ ለመጨረስ የተሰጠው ሰዓት 1 ሰዓት ነው ፡፡ ፈተናውን ሰርቶ ለመጨረስ የተሰጠው ሰዓት ሲያበቃ በፈታኙ/ኟ ትዕዛዝ መሰረት የሰራንውን ፈተና ለፈታኙ/ኟ አስረክበን ክላሳችንን ለቀን መውጣት ይኖርብናል ፡፡

1. ሀላፊነትን መወጣት ስንል ምን ማለታችን ነው?

ሀ. የሚጠበቅብንን ተግባር በአግባቡ ማሟላት ማለት ነው

ለ. ራሣችንን መጠበቅ ማለት ነው

ሐ. ለምናደርገው ነገር ተጠያቂ መሆን ማለት ነው

መ. ሁሉም

2. ከሚከተሉት ውስጥ ከግል ሐላፊነት ውስጥ የሚመደበው የቱ ነው?

ሀ, የሀገር ፍቅር ስሜት ማሳደግ ሐ, ግብር በወቅቱ መክፈል

ለ, በጓደኛ አለመቅናት መ, ህግና ደንብ ማክበር

3, ሀገራዊ ሀላፊነት ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. የግል ጤንነት መገንዘብ ሐ. ህግና ደንብ ማክበር

ለ. ግብር በወቅቱ መክፈል መ. የሀገር ፍቅር ስሜት ማሳደግ

4, የግል ሀላፊነት መወጣት የሚያመጣው አውንታዊ ውጤት ውስጥ የማይካተተው የቱ ነው?

ሀ. የቤተሰብ ደስታ ሐ. እርስ በእርስ መጋጨት

ለ. ለታናናሾች አርዓያ መሆን መ. የአዛውንቶች ምርቃት

5, ጠንካራ የስራ ባህል ምንን ይወክላል?

ሀ. እሴትን ለ. ወግን ሐ. ልምድን መ. ሁሉም

6, ጠንካራ የስራ ባህል እንደ ሀገር ምን ጠቀሜታ አለው?

ሀ. የሀገር ፍቅር ስሜት እንዲኖር ሐ. ብዝሀነትን ተቀብለን እንድንኖር

ለ. በነፃነት ለመኖር መ. ሁሉም

7, የታታሪ ሠዎች ባህሪ ያልሆነ የቱ ነው?

ሀ. በጋራ ማጥናት ለ. ስዓት ማክበር ሐ. ያልገባቸውን አለመጠየቅ መ .በክበባት መሳተፍ

8. አንድ ሠው በግብረገብ ምሉዕ ነው ሲባል ምን ማለታችን ነው?

ሀ. ታዛዥ ያልሆነ ለ. ተግባሩና ምግባሩ ሲለያይ

ሐ. ስነምግባር የጎደለው መ. ተግባሩና ምግባሩ ሲመሳሰል

9. የግብረገብ ምሉዕነት የተላበሱ ሠዎች ሊኖራቸው የማይገባ ባህሪ የቱ ነው?

ሀ. ወጥነት ለ. ሀላፊነት የሚሠማቸው

ሐ. ሀቀኝነት የጓደላቸው መ. ድፍረት ያላቸው

10. ከሚከተሉት ውስጥ ስለምሉዕነት ትክክል ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. ከሌሎች ምክር መጠየቅ ሐ. ለሌሎች ክብር መስጠት

ለ. ተለዋዋጭነት መ. ወጥነት

11, ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ የግብረገብ ምሉዕነት የተላበሠ ሠው መገለጫ ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. በራስ መተማመን ለ. ርኂራሄ ሐ. ሀቀኝነት መ. ተለዋዋጭነት

12. ከሚከተሉት ውስጥ የግብረገብ ምሉዕነት ጠቀሜታ ያልሆነውን የቱ ነው?

ሀ. የሀገርን እድገት ያፋጥናል ሐ. ስርቆት ይጨምራል

ለ. ሙሠኝነት ይቀንሳል መ. የትምህርት ጥራት ይጨምራል

13, ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ህይወታችንን በምሉዕነት ለመምራት ይጠቅማል ?

ሀ. በገንዘብ ሀብታም ሆኖ መገኘት ሐ. የቤተሰብ እርካዳታ መጠበቅ

ለ. ስኬታማ መሆን መ. ሀቀኛ መሆንና በራስ መተማመን

14, የግብረገብ ምሉዕነት ማህበራዊ ትስስርን የሚያጠናክረው

ሀ. እራሳችንን ከሌሎች በማሳነስ ሐ. በሠዎች ዘንድ እምነት ሲጣልብን

ለ. ተለዋዋጭ ባህሪን ስንላበስ መ. ስለሌሎች ችላ በማለት

15 ከሚከተሉት ምርጫ መካከል የግብረገብ ምሉዕነት አለመኖር የሚያስከትለው ችግር ምንድን ነው?

ሀ. ግብር ስወራ ለ. የሠብዓዊ መብት መከበር ሐ. ሠላም ማስከበር መ. መልስ የለም

16, በግብረ ገብ ምሉኡነት ራሳቸውን የሚመሩ ሰዎች ያሉት ማህበረሰብ  የሚያገኘው የቱ ነው?

ሀ, በሌሎተች ልፋት ጥቅም ማግኘት    ሐ, ማህበራዊ ግኑኝነት ጠንካ አለመሆን

ለ, ጠንካራ የስራ ባህል አላቸው    መ, ራሣቸው ከሌሎች አስበልጦ ማየት

17. ከሚከተሉት ውስጥ የታታሪ ተማሪ መገለጫ **<u>ያልሆነው</u>** የትኛውም ነው?

ሀ. የቤት ስራቸውን በሰአቱ ያጠናቅቃሉ

ለ. ከትምህርት ቤት ያለ አግባብ ይቀራል

ሐ. በመማር ሂደት ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ያደርጋሉ

መ. በተጓዳኝ ክበባት ይሳተፋሉ

18.ከሚከተሉት ውስጥ ስለ አሰሳ ንባብ ትክክል የሆነው የትኛውም ነው?

ሀ. የፅሁፍ አጠቃላይ ሀሳብን ለማግኘት ሲባል በፍጥነት የሚነበብ የንባብ አይነት ነው

ለ. በደቂቃ እስከ 1500 ቃላት ይነበባል

ሐ.የተወሠነ መረጃ ለማግኘት በፍጥነት ይነበባል

መ.ሁሉም መልስ ናቸው

19. ከሚከተሉት ውስጥ የጠንካራ የስራ ባህል ጠቀሜታ አይደለም?

ሀ. ከድህነት እና ከኒላ ቀርነት ለመላቀቅ

ለ. ለሀገር እድገት

ሐ. ከጥገኝነት ለመላቀቅ

መ. ተመፅዋች ለመሆን

20. ግላዊ እና ማህበራዊ አሰራሮችን ለመምራት ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ የማህበራዊ ቡድን መንፈሳዊና ቁሳዊ አካል ስብስብ ነው?

ሀ.ሀላፊነትን መወጣት    ለ.ግብረ ገባዊ ውሳኔ    ሐ. ባህል    መ.የተፈጥሮ ሀብት

21.ከሚከተሉት ውስጥ ህግን  የሚገልፀው ጽንሰ ሃሳብ የትኛውም ነው ?

ሀ.ህግ ማለት ማንኛውም ማህበረሰብ ሊከተላቸው የሚገቡ የስነ ምግባር መርሆች ናቸው

ለ.ህግ የዜጎች ይሁንታ መገለጫ ነው

ሐ.ህግ ለባለስልጣናት የተለየ ሆኖ ይዘጋጃል

መ.ሀ እና ለ መልስ ናቸው

22.በፈቃደኝነት ህግን ላለመጣስ የሚደረግ ማንኛውም እንቅስቃሴን የሚገልፀው ሀሳብ የትኛው ነው ?

ሀ.ሙስና

ሐ.ለህግ ተገዥነት

ለ.ማጭበርበር

መ.የዝምድና ወገንተኝነት

23.ከሚከተሉት ውስጥ ለህግ መገዛት አስፈላጊነት ውስጥ የማይካተተው የትኛው ነው?

ሀ.ሠላምን ለማስፈን

ሐ.ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍል

ለ.ህገ ወጥ የህፃናት ዝውውር

መ.ሙሉ ነፃነት ማግኘት

24.ለህግ ተገዥ የሆኑ ዜጎች ከሚያሳይዋቸው ባህርያቶች ውስጥ አንዱን ምረጡ?

ሀ.የመብታቸውንና ሀላፊነታቸውን ገደብ ያውቃሉ

ለ.የሀገሪቱን ህግ መጠበቅ የህዝቦችን ይሁንታ መጠበቅ እንደሆነ ያምናሉ

ሐ.ህግን አለማወቅ ከቅጣት እንደማያድናቸው ይገነዘባሉ

መ.ሁሉም መልስ ናቸው

25.ከህጎች መስፈርቶች ውስጥ የማይካተተው የትኛውም ነው?

ሀ.ቋሚ

ሐ.ተለዋዋጭነት

ለ.ወጥነት

መ. ኢ_ ፍትሃዊነት

26.ዜጎች እና የህዝብ ተመራጮች ለህግ የማይገዙ ከሆነ ምን አይነት አሉታዊ ተጽእኖ ይኖራል?

ሀ.ሉአላዊነትን ማስጠበቅ

ሐ.የሠላም እጦት

ለ.ሙሉ ነፃነት ማግኘት

መ.ሀ እና ለ መልስ ናቸው

27.ከሚከተሉት ውስጥ የሙስና መገለጫ ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ. ህግን መሠረት አድርጎ መስራት

ሐ.ጉቦ መስጠት

ለ.ማጭበርበር

መ.የዝምድና ወገንተኝነት

28. ከተሠጡን በርካታ አማራጮች ውስጥ ትክክለኛና የተሻለውን የመምረጥ እና የመወሰን ሂደት ነው?

ሀ.በራስ መተማመን

ሐ. ለህግ ተገዥነት

ለ.ግብረ ገባዊ ውሳኔ አሠጣጥ

መ. የግብረ ገብ ምሉዕነት

29. ተማሪ በረከት የ6ኛ ክፍል ተማሪ ሲሆን በመንገድ ላይ በጣም ቸኩሎ እየሄደ አስፋልት ለመሻገር የተቸገሩ አዛውንት ይመለከታል። ምን አይነት ግብረ ገባዊ ውሳኔ መወሰን አለበት?

ሀ. በጣም ስለቸኮለ እያያቸው ጥሏቸው መሄድ

ለ. እጃቸውን ይዞ ማሻገር

ሐ. ለመሄድ ያሰበበት ቦታ ይሄድና ሲመለስ ማሻገር

መ.መልሱ የለም

30. ከሚከተሉት ውስጥ የግብረ ገባዊ ውሳኔ አሠጣጥ ችሎታ ባህርያት ውስጥ የሚካተተው የትኛውም ነው?

ሀ. ምክንያታዊነት ለ. ምክንያታዊ ውሳኔ ሐ. አሳቢነት መ.ሁሉም መልስ ናቸው

31.ጥንቃቄ የተሞላበትና ስልታዊ እርምጃዎችን የሚያካትተው የግብረ ገባዊ ውሳኔ ችሎታ ባህሪ የቱ ነው ?

ሀ. አሳቢነት ለ. ምክንያታዊ ውሳኔ ሐ. ምክንያታዊነት መ. የውሳኔ አሠጣጥን መገምገም

32.ትክክለኛ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ የማይካተተው የትኛው ነው ?

ሀ. ችግሩን መለየት

ለ. መወሰን እና መከታተል

ሐ. ሊከሰቱ የሚችሉ ውጤቶችን መለየት

መ. መልስ የለም

33. ከሚከተሉት ውስጥ የግብረ ገባዊ አሠጣጥ ተግዳሮት ያልሆነውን ምረጥ ?

ሀ.የአቻ ግፊት

ሐ. የተገደበ ምክንያታዊነት

ለ. ለራስ የሚሰጥ ግምት

መ.አሳቢነት

34. ያለንን እምነት ለሚያረጋግጡ መረጃዎች ትኩረት የመስጠትና ካለን እምነት ጋር የሚጋጩ ችላ የማለት ወይም የመቀነስ  ዝንባሌ ምን ይባላል?

ሀ.  የማረጋገጫ  ወገንተኝነት

ለ. ተጨማሪ ቁርጠኝነት

ሐ. የበዛ ቁርጠኝነት

መ. የግንኙነት ግጭት

35.ሰዎች እምነቶቻቸውንና አውንታዊ አስተሳሰባቸውን በድርጊት ሲፈፅሙ ምን አይነት ባህሪ ይኖራቸዋል?

ሀ.በሠዎች ዘንድ ተቀባይነት የሌለው ባህሪ ይኖራቸዋል

ለ.መልካም ባህሪ ይኖራቸዋል

ሐ.ለህግ የማይገዛ ሰው ባህሪ ይኖራቸዋል

መ.ሀ እና ሐ መልስ ናቸው

36.ከሚከተሉት ውስጥ መልካም ባህርይ ያለው ሰው መገለጫ የሆነው የቱ ነው?

ሀ.ተጠያቂነት

ሐ.ሀቀኝነት

ለ.ምሉዕነት

መ.ሁሉም መልስ ናቸው

37.አላስፈላጊ ውስጣዊ ግፊትን፣ስሜትን እና ምኞትን መቆጣጠርን የሚገልፀው ሀሳብ የትኛው ነው?

ሀ. ሀቀኝነት  ለ. ራስን መቆጣጠር  ሐ.ትሁት መሆን  መ. በራስ መተማመን

38.የመልካም ባህሪ ባለቤት መሆን ምን አይነት ጠቀሜታ አለው?

ሀ. በህብረተሠቡ ዘንድ ክብርና ተቀባይነት ለማግኘት

ለ. በሰዎች ዘንድ እምነት ያሳጣል

ሐ.ለተለያዩ ቅጣቶች መዳረግ

መ. ሁሉም መልስ ናቸው

39.መልካም ባህርይ ማሳደጊያ መንገዶች ውስጥ የማይካተተው የትኛውም ነው?

ሀ.ኃላፊነትን መወጣት እና እራስን ለተጠያቂነት ማዘጋጀት

ለ. የግጭት ዝንባሌን ማስወገድ

ሐ. ታማኝ መሆን እና የገቡትን ቃል መጠበቅ

መ. የሰዎችን ክብር መንፈግ

40. አንድ ሰው መልካም ባህሪ ከሌለው ምን አይነት አሉታዊ ተጽእኖ ይደርስበታል?

ሀ. ብቸኛ መሆን እና መገለል

ለ. ታማኝ አለመሆን

ሐ. በቤተሠብ፣በጓደኛ እና በህብረተሠቡ ዘንድ ተቀባይነት ማጣት

መ. ሁሉም መልስ ናቸው